


# ከኦገስት 21-31 የነበረው የአየር ሁኔታ እንዲሁም

# ከሴፕቴምበር 1-10 እና ከሴፕቴምበር 11-20/2025 የሚኖረው

# የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር

2025


ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ድሬዳዋ 46.5፣ 45.1፣ ጅማ 32.8፣ መተሃራ 46.3፣ አቦቦ 57.6፣ 34.2፣ አዴት 30፣ አይራ 32.4፣ አልጌ 30፣ አምደ ወርቅ 37፣ 48.2፣ 37.5፣ አንገር ጉትን 32፣ 34.6፣ አርሲ ሮቤ 39.6፣ አሶሳ 39.8፣ አዋሽ አርባ 30፣ አየሁ 36፣ ቡለን 40፣ ቻግኒ 37.4፣ ጨዋቃ 45.2፣ 35፣ ዳንግላ 36፣ 30.6፣ ደበረ ብርሃን 38.8፣ ደበረ ታቦር 38.2፣ ዲላ 67.5፣ ኢጃጂ 85.7፣ 77.5፣ ጋምቤላ 57.5፣ ወሊሶ 34፣ ጊምቢ 49.5፣ 52.3፣ ጎሎልቻ 50፣ ሆሳዕና 32.7፣ 33.2፣ ጃራ 50፣ ጅንካ 30.7፣ ላሬ 46፣ ሊሙ ገነት 69፣ ማጂ 35.8፣ ማሻ 40.4፣ 30.6 ሞጣ 65፣ ንፋስ መዉጪያ 36.1፣ ፓዌ 65.7፣ 30.9፣ ሸርቆሌ 35.2፣ ሽሬ 30.7፣ ሲሪንቃ 43.6፣ አቦሞሪንጋ 37.2፣ 34.6፣ አዲስ ዘማን 30፣ አዲ አርቃይ 40.8፣ 50.1፣ 85.5፣ 38.4፣ 37.9፣ 30፣ 38.5፣ አቃቂ 55፣ 31፣ ቦርቃ 42.1፣ 44.6፣ ደብረ ሲና 37.6፣ ደጀን 55.8፣ ደንግጎ 31.9፣ ደራ 35.5፣ ዲንሾ 33፣ ጊናግር 35.9፣ ጉበ ይሬ 45.9፣ ሃሮ 40.2፣ 50.2፣ 52.2፣ 60.4፣ 70.2፣30.2፣ ጁሩ 48.1፣ ካራሚሌ 79.8፣ ቀርሳ 35.6፣ ቅዳሜ ገበያ 47.9፣33.8፣ ኮበን 37.5፣ ኮሶበር 30፣ ቁሉቢ 54.5፣ 37.5፣ ኩሚ 30.3፣ 42.6፣ ላሎ ቂሌ 39.2፣ ሊበን 35.2፣ ማይሃንሳ 30.1፣ መልካ ጀባዱ 61.8፣ መንደዲ 33.1፣ ሮቢት 37.3፣ ተረኮዲ 70.7፣ ትንሹ መጢ 32.6፣ ያንፋ 40.6፣ 30.3፣ 30.336.5. 32.4፣ ያዮ 31.4. መንደር 11 45፣ 39፣ የሪ 30፣ 30፣ ሲቦ 43.4፣ ዉቁሮ ማሪያ 40.3፣ 32.8፣እዳግ አረቢ 36.4፣ አንኮበር 45.1፣ 38 እንዲሁም ጎብዬ 45.6፣ 30.2 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በ76 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 52.3-85.7 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ኢጃጂ፣ አዲ አርቃይ፣ካራሚሌ፣ ተርኮዲ፣ ሃሮ፣ ሊሙ ገነት፣ ዲላ፣ ፓዌ፣ ሞጣ፣ መልካ ጀብዱ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ





ምስል፡1 ከኦገስት 21-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን እና ምዕራብ ትግራይ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ላይ ከ61-400 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-11 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ የምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ ሓረርጌ ዞኖች፤ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎ፤የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ የጋቢ_ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ጥቂት የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ እና የሊበን ዞኖች፣አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ ከ11 100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ሰሜን፣ ምዕራብ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ ባሌ፣ የምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ ሓረርጌ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎና የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ መተከል፣ አሶሳ፣ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ የጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ እና የሊበን ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የነበረው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ሁኔታ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦት ጠቀሜታ ነበረዉ፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የጎርፍ

ክስተቶች፣ የመሬት አቀማመጣቸው ከፍተኛና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተት፣ መሰንጠቅና ናዳ እንዲሁም በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛትና መጥለቅለቅ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ በተለይም በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በከምባታ ዞን በአንጋጫ ወረዳ በዞቤቾ ቀበሌ በመሬት መንሸራተት አደጋ በሰዉ ህይወት ጉዳት አድርሷል፣ እንድሁም በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በጌዴኦ ዞን በራጴ ወረዳ ለሁለት ተከታታይ ቀናት የጣለዉን ከባድ ዝናብ ተከትሎ በራጴ ወረዳ በጨራቃ ቀበሌ የመሬት ናዳ ተከስቶ በንብረትና በሰው ህይወት ላይ ጉዳት እንዳደረሰ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 4) ፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

Ethiopian Meteorology Institute

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እንዲሁም ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሀ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው አባይ፣ በላይኛው ኦሞ ጊቤ እና ተከዜ፣ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር የውሃ ሀብት መጎልበት ጥሩ አስተዋፅኦ እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ወደ ግድቦች የሚገባውን ዉሃ በመጨመር የተሻለ ውሃ እንዲይዙ ያስቻለ ነበር፡፡

የተቀሩት በአብዛኛው ኦጋዴን፣ መካከለኛ እና ታችኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በታችኛው ምስራቃዊ አዋሽ እና አፋር ደናክል አዋሳኝ ተፋሰሶች እንዲሁም በጥቂት የታችኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሆነው ቆይተዋል (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ ሴፕቴምበር የክረምት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ ከሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆነው የሰነበቱት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ማግኘት ይጀምራሉ። በዚህም መሠረት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም ከ12-23 ለሚደርሱት ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ከ3-15 ቀናት ያህል ከ20-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። የደቡብና የደቡብ ምስራቅ ስፍራዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የሚጨምር በመሆኑ 30-100 ሚ.ሜ ከ3-12 ቀናት ይደርሳል፡፡

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ወር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት ቢኖራቸው ከሰሜን ምስራቅ አከባቢዎች ላይ እየተዳከሙ የሚሄድበት ወቅት ነው፡ ፡ በመሆኑም የክረምቱ ዝናብ በስርጭትም ሆነ በመጠን ከምስራቅ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀስ በቀስ የመቀነስ አዝማሚያ የሚያሳይበት ጊዜ ነው፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በመጪዎቹ የሴፕቴምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በተለይም በምዕራብ አጋማሽ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ መካካለኛው፣ እንዲሁም በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከቀላል እስከ ከባድ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደሚኖራቸው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በበሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖረቸዋል (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በመሆኑም ከባለፉት የክረምት ወራት ጀምሮ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ በሚቀጥሉት ቀናትም ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖራል (ካርታ 6 እና 7) ፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10, , 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲ እና አርሲ፣ | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ከቀላል እስከ ከመካከለኛመጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ጌድዮ፣ እና ባስኬቶ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሀረሪ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተዳከሙ የሚሄዱበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በኃላ መልኩ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ በሌላ በኩል የክረምት ዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም የደቡብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም፣ በሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እንዲሁም መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እየጨመረ እንደሚሄድ ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

## 2.4 እ.አ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የበምስራቅ እና የመካከለኛው የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፣ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

Ethiopian Meteorology Institute

### ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ የዋግ ህምራ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ ትግራይ፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ የአኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች እድገት<br>• ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ የመኸር ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት<br>• ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የአፈር መሸርሸር<br>• የአረም መስፋፋት | • የውሃ ማንጣፈፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ አረምን በወቅቱ በማረም ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በመጠቀምና በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምዕራብ አርሲ እና አርሲ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፤ የወላይታ፣ ጎፋ፤ ጋሞ፣ጌድዮ፣ ባስኬቶ፣ ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች እድገት<br>• ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ የመኸር ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት በቂ እርጥበት መኖር<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት<br>• የአፈር መሸርሸር<br>• የአረም መስፋፋት<br>• የበረዶ ክስተት | • የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራት<br>• የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ አረምን በወቅቱ በማረም ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በመጠቀምና በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምስራቅ ሀረርጌ እና ባሌ፣የማሂ፣ ሀሪ፣ ቀልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | | • የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>• በቆላማ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሀ ማሰባሰብ |
| **በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ ዞኖችች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት መኖር | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |

## 2.5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የሴፕቴምበር የመጀመሪያው አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይጠበቃል፡ ፡ ይህም ሁኔታ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር የውኃ ይዘትን በመጨመር ወደ ሰው ሰራሽም ይሁን የተፈጥሮ የውሃ መያዣዎችና ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከፍ እንደሚያደርገውና የውሀ ሀብትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ጎን እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የገጸ ምድር የውሃ ሽፋን | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላኛው አዋሽ ፣ኦሞ ጊቤ፣ መረብ ጋሽ፣ አብዛኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ | ከፍተኛ | • የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች የውኃ መጠን ይጨምራል<br>• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይጨምራል<br>• የከርሰ ምድር የውኃ መጠን ያሻሽላል | • የወንዞች መሙላት<br>• የቅፅበታዊ ጎርፍ የመከሰት ሁኔ ሊኖር ይችላል<br>• በውሃ መያዣዎች ላይ የደለል ስጋት መጨመር<br>• የፍሳሽ መውረጃዎች በደለል እንዲሁም | • የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• ፍሳሽ ሊዘጉ የሚችሉ ቆሻሻዎች በተገቢ ሁኔታ ማስወገድ<br>• የጎርፍ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት<br>• ወራጅ ውሀን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር<br>• የዝናብ ውሀ ማሰባሰብና ማጠራቀም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን ይጨምራል | በጠጣር ቆሻሻ መዘጋት | • የጎርፍ ተጽዕኖ ትንበያዎችን ና ምክረ ሀሳቦችን በየ ጊዜው መከታተል |
| በአብዛኛው መካከለኛው እና የታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ዋቤ ሸበሌ እና ኦጋዴን | መካከለኛ | • ግድቦች የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት አይኖርም<br>• የውሃ ጥራት ይኖራል | • ዝቅተኛ የውሀ ፍሰት መኖር<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ አጥረት መከሰት<br>• ከፍተኛ ትነት መጨመር | • የሚገኘው መጠነኛ የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል በተግቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የሚገኘውን መጠነኛ የዝናበ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል |
| የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የታችኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም ኦጋዴን | ደረቅ (የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ ያልሆኑ ተፋሰሶች) | • | የውሃ መያዣዎች የውሃ መጠን መቀነስ | • አልፎ አልፎ በሚኖር ዝናብ የጣራ ላይ ውሃን ማጠራቀምና ጥቀም ላይ ማዋል |